የኢትዮጵያ የፌዴራል የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መድረክ

**Ethiopian Federal Charities and Societies Forum**

ቁጥር:
*Ref No:* 0135/EFCSF/2015
ቀን፡
Date: ሚያዚያ 14/2007 ዓ.ም

## በሊብያ ውስጥ በንጹህን ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ላይ የተፈጸመውን ኢሰብአዊ የግድያ ወንጀል በተመለከተ ከኢትዮጵያ የፌደራል የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት መድረክ የተለለፈ የሀዘን መግለጫ፣

ራሱን አይ ኤስ አይ ኤስ እያለ በሚጠራው የአሸባሪ ቡድን ሚያዚያ 11 ቀን 2007 ዓ.ም በሊብያ ውስጥ በሜዲትራኒያን ባህር አካባቢ በንጹህን የኢትዮጵያ ዜጎች ላይ ግፍ በተሞላበት ሁኔታ የተፈጸመውን አሰቃቂ ግድያ በኢትዮጵያ ውስጥ በፌዴራልና በክልል ደረጃ እየሰሩ የሚገኙ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከመላ ሰራተኞቻቸው ጋር በመሆን የተሰማቸውን ጥልቅ ልባዊ ሀዘን እየገለጹ ይህንን ኢሰብአዊ የሆነ ተግባር በአጽንኦት ያወግዛሉ፡፡ ለተመሳሰይ አደጋ ሊጋለጡ የሚችሉ ወገኖቻችንን ህይወትና ደህንነት ለመታደግና ለማስጠበቅ መንግስት የጀመረውን ዘርፈ-ብዙ ጥረት አጠነክሮ እንዲቀጥል አጋርነታችንን እየገለጽን ዜጎቻችን ለስደት የሚዳርጉ ነገሮችን ለመቅረፍ ልዩ ልዩ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ከሕዝብ እና መንግሥት ጋር በመሆን አጠናክረን ለመሥራት እንደምንፈልግ በዚህ አጋጣሚ ለማሣወቅ እንወዳለን:: ለሟች ቤተሰቦች፣ ለመንግስትና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብም መጽናናትን እንመኛለን፡፡

ነጋሽ ተክሉ
የመድረኩ ሊቀመንበር

Tele: 0118699908
E-mail: info@fcsf.net
P.O.Box:24366/1000
Fax: 0116638127